https://chilot.me

የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግስት
ደቡብ ነጋሪት ጋዜጣ
DEBUB NEGARIT GAZETA
OF THE SOUTHERN NATIONS, NATIONALITEIS AND PEOPLES REGIONAL STATE

፲፯ ዓመት ቁጥር ፪
ሀዋሳ መስከረም ፲፬ ቀን ፳፻፫/፳፻፫ ዓ.ም

በደቡብ ብሔሮች፣ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ም/ቤት ጠባቂነት የወጣ

17th Year No 2
Hawassa September 24/2010

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፭፻፴፬/፳፻፫ ዓ.ም የደቡብ ብሔሮች፣ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግስት የተርን አቨር ታክስ ማሻሻያ አዋጅ

CONTENTS

PROCLAMATION N^{o} 134/2010 The Southern Nations, Nationalities and peoples Regional Turn Over Tax Amendment Proclamation.

አዋጅ ቁጥር ፭፻፴፬/፳፻፫ ዓ.ም

የተርን አቨር ታክስን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

መግቢያ

የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ የተርን አቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር ፻፶/፲፱፻፺፭ን ከፊዴራል የተርን አቨር ታክስ ማሻሻያ አዋጅ ፮፻፲፩/፪፻፫ ጋር እና ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ ማውጣት በማስፈለጉ፣

በደቡብ ብሔሮች፣ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል መንግስት ህገመንግስት አንቀፅ ፶፩ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሰረት የሚከተለው ታውጇል።

Proclamation N^{o} 135/2010

A Proclamation to Amend The Turn over Tax Proclamation

PREAMBLE

WHERE AS, it has become necessary to amend the Regional Turnover Tax Proclamation No 57/2003 in accordance with Federal Turn over Tax No 611/2001 and in line with tangible condition of the Region;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 51 of the constitution of the southern Nation Nationalities and peoples it is here by proclaimed as follows.

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ የተርን ኦቨር ታክስ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር ፩፻፴፭/፳፻፪ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪ ማሻሻያ

የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግስት የተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር ፶፯/፲፱፻፺፭ እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

፩. የአዋጁ አንቀፅ ፮ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀፅ ተተክቷል።

፮. የተርን ኦቨር ታክስ ሰብስቦ ገቢ የማድረግ ኃላፊነት

፩. ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን የሚሸጥ ማናቸውም ሰው በሽያጩ ላይ ሊከፍል የሚገባውን ታክስ ከገዢው ሰብስቦ ለታክስ ባለስልጣን ገቢ የማድረግ ግዴታ አለበት። ስለሆነም ሻጩ ስለታክሱ የመጀመሪያ ተጠያቂ ይሆናል።

፪. የመንግስት መ/ቤቶችና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ማሕበራት ታክሱ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎችና አገልግሎቶች ሽያጭ ሲያከናውኑ የተርን ኦቨር ታክስን ከገዢው በመሰብሰብ ገቢ የማድረግ ግዴታ አለባቸው። ስለሆነም ሽያጩን ያከናወነው መ/ቤት ወይም ድርጅት ስለታክሱ የመጀመሪያ ተጠያቂ ይሆናል። የታክሱ አሰባሰብ አፈፃፀም በደንብ ይወሰናል።

1. Short Title

This proclamation may be cited as the "Turnover Tax Amendment Proclamation N°135/2010.

2. Amendment

The Turnover Tax Proclamation N° 57/2003 of the Southern, Nations, Nationalities and peoples government here by amended as follows;

1. Article 6 of the proclamation is repealed and replaced by the following new Article 6

6. Obligation to collect and Transfer the Turn over tax

1. A person who sells goods and services has the obligation to collect the Turn over Tax from the buyer and transfer the same to the Revenue Authority. Hence, the seller is accountable for the payment of the tax.

2. Governmental agencies and non governmental organizations and associations have an obligation to collect and transfer turn over tax to revenue authority when they sell goods and services which are subjects to the tax.

Hence, the government body or organization is accountable for the payment of tax. The execution of collection of the tax is to be determined by regulation.

፪. የአዋጁ አንቀፅ ፲ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀፅ ፲ ተተክቷል።

፲. **የተርን ኦቨር ታክስ ማስታወቂያ ስለማቅረብና ታክሱን ስለመክፈል**

፩. የተርን ኦቨር ታክስ ከፋዮች

ሀ. በቅይጥ ግብይት የተሰማራ ሆኖ በተጨማሪ እሴት ታክስ የመመዝገብ ግዴታ ያልተጣለበት የደረጃ «ሀ» ግብር ከፋይ የእያንዳንዱ የሂሳብ ጊዜ በተጠናቀቀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለታክስ ባለስልጣኑ ወይም ባለስልጣኑ ለሚወክለው የፋይናንስ ተቋም ወይም በኤሌክትሮኒክስ የመገናኛ ዘዴ የተርን ኦቨር ታክስ ማስታወቂያ በማቅረብ መክፈል የሚገባውን ታክስ ወዲያውኑ የመክፈል፤

ለ. ታክሱ በሚከፈልበት የንግድ ስራ የተሰማራ የደረጃ «ሐ» ግብር ከፋይ በየዓመቱ የገቢ ግብሩን ሲከፍል አንድ ላይ ለታክስ ባለስልጣኑ ወይም ባለስልጣኑ ለሚወክለው የፋይናንስ ተቋም የተርን ኦቨር ታክሱን በቁርጥ ስርዓት መሰረት የሂሳብ ጊዜው በተጠ ናቀቀ በአንድ ወር ውስጥ መክፈል የሚገባውን መጠን ወዲያውኑ የመክፈል፤

ሐ. በቅይጥ አቅርቦት ሥራ የተሰማራ ማንኛውም ሰው ታክሱን የሚሰበስበው ታክሱ በሚከፍልባቸው አቅርቦቶች ዋጋ ላይ ብቻ በመሆኑ የገቢ ማስታወቂያውን ይህንኑ በሚገልፅ ሁኔታ ማቅረብ ይኖርበታል።

መ. የታክስ ከፋዩ የተርን ኦቨር ታክስ ማስታወቂያ በሚያቀርብበት ወቅት በሂሳብ ጊዜው መክፈል ያለበትን ታክስ የመክፈል ግዴታ አለበት።

ሠ. በቅይጥ አቅርቦት የተሰማራ ማንኛውም ሰው የተርን ኦቨር ታክስ መሰብሰቢያ ደረሰኝ አጠቃቀም በተመሳሳይ የቅይጥ አቅርቦት ስራ ላይ ተሰማርተው በተጨማሪ እሴት ታክስ ለተመዘገቡ አካላት በተዘረጋው አሰራር መሰረት ይፈፀማል።

2. Article 10 of the proclamation is repealed and replaced by the following new Article 10.

10. Filing of Turn over Tax Return and payment

1. Tax payers subjects to Turn over Tax;

a. Tax payer of category “A” that is not obliged to register to value added tax and involve in mixed transaction shall file a turn over tax return and simultaneously pay to the tax Authority or to financial institution delegated by the revenue Authority or through electronic filing and payment system with in one month after the end of every accounting period.

b. Tax payer of category “ C” who involve in Taxable supply; shall pay the urn over tax with income tax payment annually to the tax Authority or to the financial institution delegated by the revenue Authority in standard system.

c. Every body which involve in mixed supply, as long as the tax is collected from the value of taxable supplies, shall submit the income declaration in the manner show the save.

d. The tax payer has an obligation to pay the tax for every accounting period at the time of filing the turn over tax return.

e. The usage of receipts of collect turn over tax for everybody involved in mixed supply shall be governed by the system established for bodies that are involved in mixed supply and registered for VAT.

፪. ለዚህ አንቀፅ አፈፃፀም «<u>የሂሳብ ጊዜ</u>» ማለት

ሀ. በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር ፸፮/ ፲፱፻፭ የደረጃ «ሀ» ግብር ከፋዮች ተብለው የሚታወቁ እና ለተጨማሪ እሴት ታክስ የመመዝገብ ግዴታ የሌለባቸው ታክስ ከፋዮች በየወሩ፤

ለ. ለመንግስት መ/ቤቶች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ማሕበራት በየወሩ፤

ሐ. በገቢ ግብር አዋጅ በተደነገገው መሰረት የሂሳብ መዝገብ ለሚይዙ የደረጃ «ለ» ግብር ከፋዮች በኢትዮጵያ የበጀት ዓመት ወይም በታክሱ ባለስልጣን ሲፈቀድ በአውሮፓ ዘመን አቆጣጠር ከዓመቱ የመጀመሪያ ቀን ጀምሮ የሚቆጠር የየሶስት ወር ጊዜ

መ. በገቢ ግብር በተደገነነው መሰረት የሂብ መዝገብ ለማይዙ የደረጃ «ሐ» ግብር ከፋዮች የበጀት ዓመቱ ነው::

፫. በአዋጁ አንቀፅ ፲፩ ላይ ያለው "በአንቀፅ ፲ ንዑስ አንቀፅ ፩ /ለ/» የሚለው ሀረግ ተሰርዞ «በአንቀፅ ፲ ንዑስ አንቀፅ ፩/መ/» በሚለው ሀረግ ተተክቷል::

4. የአዋጁ አንቀፅ ፳፩ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀፅ ፳፩ ተተክቷል::

፳፩ <u>መቀጫን ስለማንሳት</u>

፩. የታክስ ባለስልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት በታክስ ከፋይ ላይ የተጣለ አስተዳደራዊ መቀጫ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲነሳ ለማድረግ ይችላል::

፪. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ/፩/ መሰረት የሚነሳው መቀጫ በአዋጁ አንቀፅ ፳፭ መሰረት የሚታሰበውን ወለድ አይጨምርም::

2. for the purpose of this Article " Accounting period" shall mean:

a. for tax payers classified as category "A" tax payers under the income tax proclamation N^{o} 56/2003, but are not required to registered of VAT, the calendar month.

b. for governmental agencies and non governmental organization and associations per month.

c. For category "B" taxpayers who are required to keep records income tax proclamation, each three month period commencing from the first day of Ethiopian fiscal year when approved by the tax authority, the first day of the Gregorian calendar year.

d. For category "C" tax payers who are not required to keep records under Income tax proclamation the fiscal yeas.

3. The phrase "sub Article 1/B of Article 10" in Article 11 of the proclamation is repealed and replaced by the phrase sub-Article 1/d of Article 10".

4.Article 21 of the Proclamation is repealed and replaced by the following new Article 21

21. **Waived of Penality**.

1) Administrative penalties may be waived in accordance with directives issued by the tax Authority.

2). The administrative penalties to be waived in accordance with sub-article(1) of this Article may not include the interest computed in accordance with Article 25 of the proclamation.

፭. በአዋጁ አንቀፅ ፳፪ ንዑስ አንቀፅ ፪ ውስጥ «የሚፈለግበትን ተጨማሪ ታክስ ካልከፈለ» ከሚለው ሀረግ ቀጥሎ «ወይም ይግባኝ ካላቀረበ» የሚል ሐረግ ተጨምሯል።

፮. የአዋጁ አንቀፅ "፳፪ ንዑስ አንቀፅ/፫/ ንዑስ አንቀፅ ፬ ሆኖ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ ፫ ተጨምሯል።

፳፪(፫)ታክስ ባለስልጣኑ ሰራተኛ ያለበቂ ምክንያት ጉዳዩን በማጓተት በግብር ከፋይ ላይ ለሚያደርሰው ጉዳት በፍትሐብሔር ያለበት ሃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ ጥፋተኛነቱ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከአንድ ዓመት እስከ ሁለት ዓመት በሚደርስ እስራት ይቀጣል።

፯ <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በደቡብ ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ህዋሳ መስከረም ፲፬ ቀን ፳፻፫
ሽፈራው ሽጉጤ
የደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መንግስት
ርዕሰ መስተዳድር

5. The phrase “or appealed against it decision” is added before the phrase” with in thirty(30) days” in sub-article (2) of Article 22 of the proclamation.

6. Sub- article (3) of Article 31 of the proclamation is re-numbered as sub-article (4) and the following new sub-article (3) is added.

31(3). The Authority’s officer shall be held responsible for any damage caused to a tax payer by delaying, without any good cause, the performance of his/her duty such employee in addition to being held liable for the damages, shall, upon conviction, be punished with imprisonment for a term of not less than one year and not more than two years.

7. Effective Date

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Debub Negarit Gazeta

Done at Hawassa sep /2010
Shiferaw Shigutie
President, Southern Nations ,Nationalities and Peoples Regional State